ሁኔታ ጠቅላላውን የወንጀል ሕጉን መሠረታዊ ግብ መነሻ በማድረግ ቅጣቱ መገደብ የለበትም ከሚለው መደምደሚያ ላይ መድረሱ የወንጀል ቅጣት አወሳሰንና አፈፃፀም የወንጀል ሰሪውን ልዩና ግላዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ መሆን አለበባቸው በማለት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 41 የተቀመጠውን መሠረታዊ መርህ የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም ቅጣትን መገደብን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ግምት ውስጥ በማስገባትና በሕግ የተደረገውን ክልከላ ሣይተላለፍ፣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቅጣቱን በመገደብ የሰጠውን ትዕዛዝ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በመሻር የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ስለሆነም ይህ ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ አመልካች ያልፈፀመው ቀሪው፣ የእስራት ቅጣት በሶስት ዓመት ሊገደብለት ይገባል በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. አመልካች ያልፈፀመው ቀሪው የእስራት ጊዜ በሶስት ዓመት የሙከራ ጊዜ የተገደበለት መሆኑን አውቆ፣ ከእስር እንዲለቀቀው አመልካች እስሩን እየፈፀመበት ላለው ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣቱን አፈፃፀም አስመልክቶ፣ የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአዳሪ ሲሰራ ቆይቶ ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 34521

ሰኔ 3 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን እቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

**አመልካች፡-** የአማራ ብ/ክ/መ/ ፍትሕ ቢሮ

**ተጠሪ፡-** ስንታየሁ ተፈራ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ተጠሪ በሰው ላይ የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽሞአል በሚል የቀረበውን ክስ መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክሱን የሰማው የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ በቅድሚያ የተጠሪን የእምነት ክህደት ቃል ከተቀበለ በኋላ ተጠሪ ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለቱ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡትን ምስክሮች ሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪ እንዲከላከል ብይን በመስጠት የመከላከያ ምስክሮችን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ተጠሪ ወንጀሉን ላለመፈጸሙ በመከላከያው አስረድቶአል በማለት በነፃ አሰናብቶታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዓቃቤ ሕጉ ውሣኔውን በመቃወም ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ ከዚህ በኋላም ፍ/ቤቱ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሣኔ በመሻር ተጠሪ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ነው ብሎአል፡፡ ለጥፋቱ ይመጥናል ብሎ ባመነው መሠረትም ተጠሪ በስድስት /6/ ወር እስራት እንዲቀጣ ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ታህሣሥ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በወ/መ/ሕግ ቁ. 27/1/ እና 523 የተመለከተለውን ድንጋጌ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሞአል በሚል ጥፋተኛ የተባለውን ተጠሪ በስድስት /6/ ወር እስራት እንዲቀጣ የተወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ተጠሪ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎአል፡፡ ጥፋተኛ የተባለበት የወ/መ/ሕግ ቁ. 523ም የሚያስቀጣው ከአምስት /5/ ዓመት በማያንስ ከሃያ /20/ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ነው፡፡ በእርግጥ ጥፋተኛ በተባለ ተከሣሽ ላይ ቅጣት ሲወሰን /ሕጉን መሠረት ያደረጉ/ የተለያዩ የማክበጃም ሆነ የማቅለያ ምክንያቶችን እግምት ውስጥ በማግባት በመሆኑ እንደ ሁኔታው ቅጣቱ ሊቀልም ሊከብድም የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የቅጣቱ መነሻ በሕጉ በግልጽ ተቀምጦአል፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ የወሰነው ቅጣት ግን ከመነሻው ወርዶ /ዝቅ ብሎ/ ስድስት ወር ሆኖአል፡፡ አከራካሪ ሆኖ የቀረበውም ፍ/ቤቱ ይህን ያሕል ዝቅ ብሎ ለመውረድ የሚያስችለው የሕግ ምክንያት ነበረው ወይ? የሚለው ነው፡፡

ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ለማቅለል ይችል ዘንድ በዋቢነት የጠቀሰው የወ/መ/ሕግ ቁ. 184/መ/ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ቁጥር 184 ቅጣትን ለማቅለል የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች በዝርዝር የያዘ ሲሆን፣ ይህም ከፍተኛው ቅጣት ማለትም ከሞት ቅጣት ነው የሚጀምረው፡፡ የሞት ፍርድን ከሃያ /20/ ዓመት እስከ እድሜ ልክ ጽኑ እስራት፣ የእድሜ ልክ እስራትን ከአስር /10/ ዓመት እስከ ሃያ /20/ በሆነ ጽኑ እስራት ማቃለል እንደሚቻል በንኡስ አንቀጽ /ሀ/ እና /ለ/ የተመለከተ ሲሆን፣ የእስራቱ ቅጣት መነሻ ከፍ



ብሎ በተለይ የታዘዘ ከሆነ ደግሞ ቅጣቱን ዝቅ ማድረግ የሚቻለው ከአንድ /1/ ዓመት ጀምሮ እንደሆነ በንኡስ አንቀጽ /ሐ/ ተመልክቶአል፡፡ በወ/መ/ሕግ ቁ. 107 እንደተደነገገው ጽኑ እስራት የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ዓመት እስከ 25 /ሃያ አምስት/ ዓመት ቢሆንም፤ በሕጉ ልዩ ክፍል የቅጣቱ መነሻ ከአንድ ዓመት በላይ ከፍ ብሎ ከተወሰነ ግን በሕጉ አግባብ ያላቸው የማቅለያ ምክንያቶች ካልተገኙ በቀር እንደመነሻ የሚያዘው ይኸው በልዩ ክፍል የተመለከተው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይም ቅጣቱ መወሰን ያለበት በዚህ መሠረት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የጠ/ፍ/ቤቱ እግምት ውስጥ ያስገባቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተጠሪ ላይ ሊወሰን የሚችለው ቅጣት ከአንድ /1/ ዓመት በታች ሊወርድ የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ ውሣኔ በሰጠበት ጊዜ ሥራ ላይ በነበረው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 179/ሐ/ እንደተመለከተውም የጽኑ እስራቱ ቅጣት መነሻ ከፍ ብሎ በሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ በዚህ ቅጣት ምትክ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል መነሻ ሆኖ ከተደነገገው ከአንድ ዓመት ጀምሮ የጽኑ እስራት ቅጣት ሊወሰን እንደሚቻል ነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1.አቤቱታ የቀረበበት በአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 103/98 ኀዳር 4 ቀን 2000 ዓ.ም. የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕግ ስ/ስ/ቁ. 195/2/መ/ መሠረት ተሻሎአል፡፡

2.ተጠሪ በአንድ /1/ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡ ይኸው ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡

3.መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ